# ገጹኩ
# ወርቅ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቦች የተወሰዱት
በ1954 ከታተመው
የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

# የእግዚአብሔር ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ቃላት

2022 / 2014 E.C. Edition
© by GBV
printed in Germany

**GBV Dillenburg GmbH**
Eiershäuser Straße 54
35713 Eschenburg
GERMANY
www.gbv-dillenburg.de
www.gbv-online.org

በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥
ቃልም በእግዚአብሔር
ዘንድ ነበረ፥
ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።
*ዮሐንስ 1:1*

በእርሱ ሕይወት ነበረች፥
ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።
*ዮሐንስ 1:4*

ኢየሱስ፡-
“እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤
የሚከተለኝ የሕይወት
ብርሃን ይሆንለታል እንጂ
በጨለማ አይመላለስም”
ብሎ ተናገራቸው።
*ዮሐንስ 8:12*



“እኔ
መንገድና እውነት
ሕይወትም ነኝ፤
በእኔ በቀር ወደ አብ
የሚመጣ የለም።”
*ዮሐንስ 14:6*

ኢየሱስ ቆሞ፡-
“ማንም የተጠማ ቢኖር
ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ።
በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥
የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ
ይፈልቃል” ብሎ ጮኸ።
*ዮሐንስ 7:37-38*



“እናንተ ደካሞች
ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥
ወደ እኔ ኑ፥
እኔም አሳርፋችኋለሁ።”
*ማቴዎስ 11:28*

“ቀንበሬ ልዝብ
ሸክሜም ቀሊል ነውና።”
*ማቴዎስ 11:30*

አምላክ ሆይ፡-
እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ!
*ሉቃስ 18፡13*

የኃጢአት
ደመወዝ ሞት ነውና፤
የእግዚአብሔር የጸጋ
ስጦታ ግን በክርስቶስ
ኢየሱስ በጌታችን
የዘላለም ሕይወት ነው።
*ሮሜ 6:23*



ኢየሱስም መለሰ፡-
“እውነት እውነት እልሃለሁ፥
ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር
የእግዚአብሔርን መንግሥት
ሊያይ አይችልም” አለው።
*ዮሐንስ 3:3*

“ዳግመኛ
ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል
ስላልሁህ አታድንቅ።”
*ዮሐንስ 3:7*

ኃጢአታችሁ
ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ
ግቡ ተመለሱም።
*የሐዋርያት ሥራ 3:19*

በኃጢአታችን
ብንናዘዝ ኃጢአታችንን
ይቅር ሊለን ከዓመፃም
ሁሉ ሊያነጻን
የታመነና ጻድቅ ነው።
*1ዮሐንስ 1:9*



ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥
በስሙ ለሚያምኑት
ለእነርሱ የእግዚአብሔር
ልጆች ይሆኑ ዘንድ
ሥልጣንን ሰጣቸው፤
እነርሱም
ከእግዚአብሔር ተወለዱ ...
*ዮሐንስ 1:12-13*

"እውነት እውነት እላችኋለሁ፥
ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም
የሚያምን የዘላለም
ሕይወት አለው፥
ከሞትም ወደ ሕይወት
ተሻገረ እንጂ ወደ
ፍርድ አይመጣም።"
*ዮሐንስ 5:24*



"በእርሱ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም
ሕይወት እንዲኖረው
እንጂ እንዳይጠፋ
እግዚአብሔር አንድያ
ልጁን እስኪሰጥ
ድረስ ዓለሙን
እንዲሁ ወዶአልና።"
*ዮሐንስ 3:16*

እርሱ ግን ስለ
መተላለፋችን ቈሰለ፥
ስለ በደላችንም ደቀቀ፤
የደኅንነታችንም ተግሣጽ
በእርሱ ላይ ነበረ፥
በእርሱም ቍስል
እኛ ተፈወስን።
*ኢሳይያስ 53:5*



"እነሆ በደጅ
ቆሜ አንኳኳለሁ፤
ማንም ድምፄን ቢሰማ
ደጁንም ቢከፍትልኝ፥
ወደ እርሱ እገባለሁ።"
*ራእይ 3:20*

... ክርስቶስም
በልባችሁ በእምነት እንዲኖር ...
*ኤፌሶን 3:17*

"የሰው ልጅ
የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን
መጥቶአልና አለው።"
*ሉቃስ 19:10*

"ወደ እኔም
የሚመጣውን ከቶ
ወደ ውጭ አላወጣውም"
*ዮሐንስ 6:37*



አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ
*ሉቃስ 14:17*

እድን ዘንድ
ምን ማድረግ ይገባኛል?
... በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ እመን፣
አንተና ቤተ
ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።
*የሐዋርያት ሥራ 16:30-31*

በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።

*የሐዋርያት ሥራ 10:43*

ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠው እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣው ጌታንችን ኢየሱስ ...።

*ሮሜ 4:24-25*



እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም።

*ሮሜ 8:1*

የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ

*1ዮሐንስ 5:13*

"ስማችሁ ግን
በሰማያት ሰለ ተጻፈ ደስ
ይበላችሁ።"
*ሉቃስ 10:20*

እንግዲህ በእምነት
ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ሰላምን እንያዝ፤
*ሮሜ 5:1*



ጸጋው
በእምነት አድኖአችኋልና፤
ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
ማንም እንዳይመካ
ከሥራ አይደለም።
*ኤፌሶን 2:8-9*

ስለማይነገር
ስጦታው እግዚአብሔር
ይመስገን።
*2ቆሮንቶስ 9:15*

ነገር ግን እርሱ
በብርሃን እንዳለ
በብርሃን ብንመላለስ
ለእያንዳንዳችን
ኅብረት አለን፥
የልጁም የኢየሱስ
ክርስቶስ ደም ከኃጢአት
ሁሉ ያነጻናል።
*1ዮሐንስ 1:7*



"በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ
እኔም አውቃቸዋለሁ
ይከተሉኝማል፤
እኔም የዘላለም ሕይወትን
እሰጣቸዋለሁ፥
ለዘላለምም አይጠፉም፥
ከእጄም ማንም
አይነጥቃቸውም።"
*ዮሐንስ 10:27-28*

ክርስቶስ ደግሞ
ፍለጋውን እንድትከተሉ
ምሳሌ ትቶላችሁ
ስለ እናንተ መከራን
ተቀብሎአልና።
*1ጴጥሮስ 2:21*



"እነሆም እኔ
እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ
ከእናንተ ጋር ነኝ።"
*ማቴዎስ 28:20*

"መልካሙን
ሥራችሁን አይተው በሰማያት
ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ
ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው
ፊት ይብራ።"
*ማቴዎስ 5:16*

"በእኔና
በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥
የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና
በቅዱሳን መላእክቱ
ክብርም ሲመጣ
በእርሱ ያፍርበታል።"

*ሉቃስ 9:26*



ሣሩ ይደርቃል
አበባውም ይረግፋል፥
የአምላካችን ቃል ግን
ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

*ኢሳይያስ 40:8*

"ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ
ግን አያልፍም።"

*ሉቃስ 21:33*

በነገር ሁሉ
በጸሎትና በምልጃ
ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር
ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ
እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።
አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ
የእግዚአብሔር ሰላም
ልባችሁንና አሳባችሁን
በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።
*ፊልጵስዩስ 4:6-7*



በዘላለም
ፍቅር ወድጄሻለሁ፤
ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ።
*ኢሳይያስ 41:10*

እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ
*ኤርምያስ 31:3*

“ስፍራ አዘጋጅላችሁ
ዘንድ እሄዳለሁና፤
ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥
እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ
እንድትሆኑ ሁለተኛ
እመጣለሁ ወደ እኔም
እወስዳችኋለሁ።
*ዮሐንስ 14:2-3*



ጌታ ራሱ ...
ከሰማይ ይወርዳልና፥
በክርስቶስም የሞቱ
አስቀድመው ይነሣሉ፤
ከዚያም በኋላ እኛ
ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥
ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ
ጋር በደመና እንነጠቃለን፤
እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ
ጋር እንሆናለን።
*1ተሰሎንቄ 4:16-17*

አዲስ ሰማይንና
አዲስ ምድርንም አየሁሁ
*ራእይ 21:1*

እንባዎችንም
ሁሉ ዓይኖቻቸው ያብሳል፥
ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥
ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት
ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ
ወዲህ አይሆንም፥
የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና።
*ራእይ 21:4*



እነሆ፥
በቶሎ እመጣለሁ፥
*ራእይ 22:12*

የተጠማም ይምጣ፥
የወደደም የሕይወትን ውኃ
እንዲያው ይውሰድ።
*ራእይ 22:17*

አሜን፥
ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና!
*ራእይ 22:20*

መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ፣
የእግዚአብሔር ቃል ነው።
የእግዚአብሔርን ድምፅ ስማ።
ታላቁ ሕያው እግዚአብሔር
ስለአንተ ግድ ይለዋል።
እርሱ ይህን ፍቅሩን እንድታውቅ
ይፈልጋል። ወደ እውነተኛ ዕረፍት፣
ወደ እውነተኛ ደስታና ሰላም
የሚወስደውን መንገድ በቃሉ
ውስጥ ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌለህ
በጠየቅህ ጊዜ አዲስ ኪዳንን
(2ኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል)
በነጻ ልንልክልህ እንወዳለን።

ማናቸኛውም ጥያቄዎች ካሉህ ደስ
እያለን ልንመልስልህ እንችላለን።

GBV 115 4120 Pure Gold Amharic